

# ዛሬ ሁላችንም ግንቦት ሰባት ነን !

Million Shiferaw- Norway

ኢትዮጵያዊነት ማተብ ነው፣ በአካልና መንፈስ ፅናት፣
በአበው ታሪክ አምኖ መኩራት ፡፡
ኢትዮጵያዊነትን መክዳት፣ የፍቅር አምላክን ሲሳይ፣
መርገጥ ነው እንደ እኩይ ጠባይ፣
የአንድነት አድባር ፈንግሎ፣ ለመናፍቃዊ ግዳይ፣
በትውልድ ላይ ሰቆቃ፣ የአካልና መንፈስ ስቃይ፣
ማንገሥ ብቻ ነው ውጤቱ፣ በራስም ላይ በህዝብም ላይ ፡፡
የኢትዮጵያዊነት መሥፈርቱ፣ ነጻነት ነው ላንድ ዜጋ፣
መንፈሳዊ ነው እሴቱ፣ የማይዳሸቅ ለስጋ፣
የማይገብር ለጠመንጃ፣ የማይተመን በዋጋ፣
መንፈሱን ቆርሶ ለመሸጥ፣ ሳይሆን እንደ ባንዳ መንጋ ፡፡
ወይ እንደትላንቶቹ ፣ ለዙፋን ባርነት ሳይሆን፣
ወይ ለጦር መኮንኖች ምርጥ ፣ ለማጎብደድ ለአንድ ሰሞን ፡፡
ኢትዮጵያዊነት ክብር ነው፣ ለኃያል ክንድ የማይዳር፣
ሕዝባዊነት ነው መስፈርቱ፣ የሕዝብ ወገን የህዝብ አጋር፣
እንጂ፣ለዘረኞች ቁማር፣ ለአንድ ጎሳ ቡድን ገባር፣
ሊሆን እንደሚጣል ዕጣ ፣ አይደለም ሎተሪ ቢጋር ፡፡

« ኢትዮጵያዊነት »-ከሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን ግጥም የተወሰደ ፡፡

ልክ የዛሬ ሶስት ዓመት እንደፈረንጆቹ የወር አቆጣጠር በወርሃ ሃምሌ በኖርዌይ ዋና መዲና በኦስሎ ከተማ አንድ ሽብር ተካሄደ ፡፡ ይህ ብራይቪክ የተባለ ጽንፈኛ የኖርዌይ ዜጋ ፣ የጠቅላይ ሚንስትሩን ቢሮ በቦምብ በማጋየትና እንዲሁም ኡተያ ተብላ በምትጠራ ደሴት ፣ ታዳጊና ተተኪ የሆኑ የሌበር ፓርቲ ተከታዮች አመታዊ ጉባኤያቸውን እያካሄዱ ባለበት ወቅት፣ ይህ አሸባሪ ሰው ቁጥሩ እጅግ የበዛ ነብስ በመትረየስ አጠፋ ፡፡ ይህን ግዜ ነው በኖርዌይ ያሉት ከአምስት በላይ ያሉ ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ፣ የየፓርቲያቸውን ማልያ አውልቀው ፣ ዛሬ ሁላችንም የሌበር ፓርቲ ነን ያሉት፡፡

እንደ አጋጣሚ ሆኖ አቶ አንዳርጋቸውን በኖርዌይ የስደት ዘመኔ ሶስት ጊዜ አይቸዋለሁ ፡፡ አንተ ስለው አንድም በመውደድና በማክበር ሲሆን ፣ በሀገራችንም ባህል ጀግናን የምናወድሰው አንተ እያልን ስለሆነ እንጂ ፣ ይህን ጀግናችንን እኔ አንድ ትንሽ ዜጋ ክብሩን ለማሳነስ ብዬ አይደለም ፡፡ አቶ አንዳርጋቸው ከምርጫ 97 በኋላ ወደ ኖርዌይ ኦስሎ መጥቶ ገለጻ ባደረገበት ወቅት አንድ ታዳሚ ስለህወሃቶችና ፣ በተለይም በውጭ ያሉ የትግራይ ተወላጆች ከስርዓቱ ጋር ስላላቸው ፍቅርና ፥ በሌሎች ብሄሮች ላይ ስላላቸው ንቀት እንዲሁም ዋልጌነት አንስቶ ሲጠይቀው ፣ አቶ አንዳርጋቸው ሲቃ ይዞት እንባውን ማቆር አቅቶት በሲቃ አንድ በኢትዮጵያውያን ባህል በተለበጠች አባባል አንድ ነገር ተናገረ ፡፡

በስድሳዎቹ ውስጥ እነደማንኛውም ነጻነት ፈላጊ ወጣት ፣ ፋኖ ሆኜ የኢህአፓን ሠራዊት በመቀላቀል ትግራይ ውስጥ አሲምባ በምትባል ቦታ የደርግን ስርአት እታገል ነበር ፡፡ በዚያን ወቅት ትግርኛን ቋንቋ በደንብ አድርጌ መስማት ችየ ነበር ፡፡ ስለዚህ ትግርኛን በደንብ አድርጌ አሁንም እሰማለሁ ፡፡ በምርጫ 97 ወቅት ወያኔ ወደ እስር ቤት ሊወርውረኝ ከቤተሰቦቼ ቤት ውስጥ ሊወስደኝ ሲመጣ ፣ ከሾፌሩ ጀምሮ እስከ ታጣቂዎቹ ድረስ ፣ በሙሉ ትግርኛ ተናጋሪዎች ነበሩ ፡፡ በዚያን ወቅት በትግርኛ የሚነጋገሩትንና የሚሳደቡትን ስድብ በሙሉ አደምጥ ነበር ፡፡ አንቋሸው ብሄሬን ሲሳደቡ ከድብደባቸው በላይ የተሰማኝ ህመም ያኔ ነበር ፡፡ እንደነርሱ ግን ባልተሞረደ ቋንቋ ያንን ስድብ ይህ ጉባኤተኛ እንዲሰማው ባህሌም ሆነ ቋንቋዬ አይፈቅድም ነበር ያለው፡፡

ወያኔ በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የበቀል ርምጃውን የጀመረው ዛሬ አይደለም ። ልጆቻቸውን ሊጠይቁ ወደ እንግሊዝ አገር መጥተው በነበሩት አዛውንት ወላጅ አባቱ ላይ ጭምር ግፍ ሰርቶባቸዋል ። ጉብኝታቸውን ጨርሰው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ሻንጣ ገልብጠው ፣ ከሻንጣቸው ውስጥ የግንቦት ሰባት በራሪ ወረቀት በመከተት፣ በራሪ የግንቦት ሰባት ወረቀት ይዘው መጥተዋል በሚል ተልካሻ የጫካ ውስጥ ውንብድና ነበር አዛውንቱን ሃብትና ቤታቸውን በመውረስ ቃሊቲ የወረወሯቸው ። ህግና ፍርድ ቤት በለለበት አገር አዛውንቱን ለአመታት እስር ቤት ውስጥም ቆልፈውባቸው ነበር ።

የስርአቱ ደጋፊዎችና በወያኔ ቅንጥብጣቢ ጥቅም የታወሩ ሰዎች ይህን የተደረገ እኩይ ድርጊት ስጽፍ ምናልባት ቀልድ ሊመስላቸው ይችል ይሆናል ። ወያኔ እንኳን ከሚያስተዳድረው የቦሌ ኤርፖርት ቀርቶ ፣ እጁ ረዝሞ የመን ሰንአ ኤርፖርት ድረስ በመዝለቅ ጨልሌነቱን አስመስክሯል ። የነጻነት ታጋያችንን ጨልፎ ውስዶብናል ። ለዚህ ማሳያ ዶ/ር መረራ ጉዲና « የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞ ብለው ካሳተሙት መጽሃፍ ላይ » ፣ ወንበዴው መንግሥት ነኝ ባይ የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት የፈጸመውን አሳፋሪ ድርግት ካነበብኩት ላይ ለንፅጽር ላቅርብ ።

መረራ እንዲህ ይተርካሉ ። ቦሌ ላይም ሁለት ያልጠበኩት ነገሮች ገጥመውኛል ። አንደኛው የአውሮፓ ፓርላማ ከዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጋር ጋብዞኝ ልሄድ ስል ፣ የመነሻ ሰዓቴን በመደበቅ አውሮፕላን እንዲያመልጠኝ አድርገዋል ። በኔ ፋንታ ዶክተር ነገደ በህብረት ስም ንግግር ስላደረገ እራሳቸው ተመልሰው በሽቀዋል ። ሁለተኛው ሻንጣዬን ቦሌ ላይ ደህንነቶች ሰርቀው ፣ ስሜን በሌላ ሻንጣ ላይ ለጥፈው ወደ ውጭ ልከዋል ። እስቶክሆልም ደርሼ ሻንጣዬን አጣሁ ። ስሜ የተለጠፈበት ሻንጣ ውስጡ ምን እንዳለ ያለማየቴ እስከአሁን ይቆጨኛል ። ሉፍታንዛ የእቃዬን ዋጋ አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር ስለከፈለኝ አልተጎዳሁም ። ከወራቶች በኋላ አንዱ ሰው ለሌላው እየነገረ ደህንነቶች ቦሌ ላይ ሻንጣዬን ሊወስዱ የሉፍትሃንዛዋ ሃላፊ ፣ ፍተሻ ያለፈ ሻንጣ አትወስዱም ብላ ስትጨቃጨቅ እንደነበር ሰማሁ ። የኢህአዴግ ደህንነቶች ምን ያህል እንደሚሄዱ በዛው አውቅሁ ። ይላሉ መረራ በመጽሃፋቸው ላይ ። ይህን በቦሌ የሚሰራውን ግፍ ታሳቢ በማድረግ ፣ ወያኔ በጸረ ወያኔነት የሚያውቀውን ሰው ይቅርና ዝምድናና ንክኪ ያለውን ሰው ሳይቀር ሻንጣ ከመከርበት እንደማያልፍ የሚያረጋግጥ እውነታ ነው ። የማፍያ መንግስት ስለሆነ ለመንግሥቱ ስጋት ናቸው ያላቸውን ሰዎች ሻንጣ ጭምር እፍኝ ማርያዋና ኮኬይን በሻንጣ ውስጥ አስቋጥሮ በመላክ ሰውን በውጭ አገር እስከማስያዝ ሊደርስ የሚችል መንግሥት እንደሆነ የመረራ መጽሃፍ ያረጋግጣል ።

ይህ የውንብድና ሥራ በአቶ አንዳርጋቸው ወላጅ አባት ላይ ተፈጽሟል ። ወያኔዎች እንኳን በሚገዙትና በሚረግጡት አገር ይቅርና ሰንአም ላይ ጡንቻቸውን አሳይተዋል ። ወደ አገር ዘመድ ሊጠይቅ የሚያቀናው ዜጋ ሁሉ ዋስትናው ምን እንደሚሆን አይታወቅም ። ሥርአቱን የጠሉ ፣ወይም ይጠላሉ ተብለው የሚገመቱ ሰዎች ከዚህ ጠለፋ ያመልጣሉ ብሎ ማሰብም በፍጹም አይቻልም ። ወያኔ እንኳን የኢትዮጵያን አየር መንገድን ይቅርና የውጭ አየር መንገዶችን ጭምር እጅ በመጠምዘዝ የአለም አቀፍ ህግጋትን በመጣስ ሻንጣ ከርባችነቱን ያረጋገጠ መንግስት ነው ። የበረራ ደህንነትን መብት በመጣስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሊጓዙ የተመዘገቡ ስሞችን ህግ ከሚፈቅደው ውጭ ፣ ቀድሞ በመውሰድ እያጣራ ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ላይ በመጠበቅ ፣ የፈለገውን ሰው ነጥሎ በመውሰድ አሻራ በመውሰድ ማስፈራራትና ማሸበሩን ከተያያዘው ቆይቷል ።

ወያኔ የምኒልክ ቤተመንግሥቱን ስልጣን ለመጠበቅ ሲል በሌላ በኩል አገሪቱ ለዘመናት በማንበር ያቆየችውን የኢትዮጵያ አየር መንገድን ዝናና ክብር በመናድ ከስልጣኑ ውጭ ደንታው እንዳልሆነም በአሁኑ ወቅት ከቁንጮው እስከ ታች ድረስ የሰገሰጋቸው ማይማን የህወሃት ካድሬዎቹ ማሳያ ናቸው ። አቶ አንዳርጋቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ ትንሳኤ ሲል ወንድሙን ለቀይ ሽብር ፥ ወላጅ አባቱን ለእስር ፥ የርሱን ውድ ህይወት ደግሞ ለህዝባችን ሲል ቤዛ አድርጓል ። አንዳርጋቸው በዚህ ወቅት ህጻናት ልጆቹን ከሶፋ ላይ አድርጎ ፣ ቺፕስና ኮካ እየተጎነጩ ፣ የአርጀንቲናን ቤልጅግን ቀጥሎም የሆላንድንና ፥ ኮስታሪካን በተከታታይም ለፍጻሜው ዋንጫ የሚያልፉትን የአለም ዋንጫን ጨዋታ ሆ ! እያለ እንደሌሎቻችን ማየት ይችል ነበር ። ግን ኮከቡ ሆነና ፥ ግፍና መከራን ወገኑ ሲጎነጭ ማድመጥ ስላቃተው በማረፊያ እድሜው እንደ አጼ ቲዎድሮስ መድፍ ሽቅብ ቁልቁል ሲልና ፣ ለናት አገሩ ሲዋትት ፣ በነብሰ ገዳዮች እጅ ወደቀ ።

አንዳርጋቸው ሎሬት ጸጋዬ በአንድ ወቅት እንደከተቡት ፣ ከሴት ታኮ ስር ወድቆ አይደለም የተገኘው ።የሰው ቁስል ሲያክም ፣ለራሱ ህይወት ሳይኖር ነው ለሁላችንም ቤዛ የሆነው ። ጩኸታችን የአንድ ሰሞን መሆን የለበትም ። ድንኳን ጥለን ለቅሶ ላይ ነን ። ሰልስት ላይ ተለቃቅሰን ድንኳን አፍርሰን የምንለያይበት ወቅት አይደለም ። እንደቀድሞውም አስወስደን መጣን የሚለውን ሙሾ አውርደን የምንለያይበትም ወቅት አይደለም ። አንድ ድርጊት ሲፈጸም በፓልቶክ ክፍል ውስጥ ቁጥር እስኪጠብ ድረስ ሁሉም ቃልቻ ማን ይሸከማል ስልቻ ሆኖ ሁሉም ተንታኝ፣ ሁሉም አውሪ የሚሆንበትም ወቅት አይደለም ። ቱቢታችንና ከል ልብሳችን አገራችን ከእፍኝ ዘረኛ ወንበዴዎች አገዛዝ ስር

እስከትላቀቅ ድረስ ፥ አስከንድር ፥ አንዷለም ፥ ርዕዮት ፣ውብሸት ፣ በቀለ ገርባ ፥ ዕልፍ አእላፍ የፖለቲካ እስረኞች እስኪለቀቁ ድረስ ከሰውነታችን ላይ መውረድ የለበትም ፡፡ ዛሬም ነገም ኢትዮጵያ ነጻ እስከምትወጣ ድረስ ሁላችንም ግንቦት ሰባት ነን ፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!

ሚልዮን ሽፈራው / ኖርዌይ